# የስንኝ ቋጠሮ

(ከአብርሃም   በየነ)

የዛሬ ዘመን ገበሬ፣

ማረስ አቅቶት በበሬ።

ለቀን መውጫዬ ብሎ፣

ሰናፍጭ ጎመን አትክሎ።

የክህደት ዘመን በመሆኑ፣

ለማገው ሙዙና ብርቱካኑ።

ፍሬ አልባ ሆነው መከኑ!

አምራቹን ሀይል ርሀብ ሲለጋው፣

አንጀቱ ደርቆ ጎኑን ጎኑ ሲወጋው፣

ምላሱ ተጣብቆ ከትናጋው።

ብርሀኑም ክዶት አብሎ፣

ቀኑ ከሌሊቱ ተመሳስሎ።

አይኑን ገርሞት ያለድሜው፣

ተስፋውን ጉም አዘጋው!

ነገን መጠበቅ በጥሞና፣

የድሃ ተስፋው ሆነና።

ተስፋውን ሰንቆ አድሮ፣

ያቅሙን ያክል ቆፋፍሮ።

ሰኔ ሲደርስ ግንቦት፣

ዘር ሳይዙ መሬት ሆነበት!

Posted on www.debteraw.com by courtesy of the author

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com